የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

# በንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

## በቱሪዝም ሚኒስቴር የ2014 ዓ/ም የ6 ወራት አፈፃፀም ሪፖርት ላይ

## የተሰጠ ግብረ መልስ

ጥር 2014 ዓ.ም

# በንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

# በቱሪዝም ሚኒስቴር የ2014 ዓ/ም የ6 ወራት አፈፃፀም ሪፖርት ላይ

# የተሰጠ ግብረ መልስ

## መግቢያ

በኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተግባሩን በአግባቡ ለመወጣት ያስችለው ዘንድ በተሻሻለው የውሳኔ ሃሳብ ቁጥር 3/2014 መሰረት 11 ቋሚ ኮሚቴዎችን ያደራጀ ሲሆን የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴም በዚህ መሠረት መቋቋሙ ይታወቃል፡፡ ቋሚ ኮሚቴው ከሚከታተላቸው አስፈጻሚ መ/ቤቶች አንዱ ቱሪዝም ሚኒስቴር ሲሆን ከተቋሙ የተላከውን የ2014 ዓ.ም የ6 ወራት አፈፃፀም ሪፖርት መሰረት በማድረግ በጥንካሬ፣ በዕጥረትና እንዲሁም ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና ጉዳዮችን በመለየት የሚከተለውን ግብረ መልስ ሰጥቷል።

## በጥንካሬ የታዩ ዋና ዋና ጉዳዮች

- አዲስ በተቋቋመው ክልል ማለትም በሲዳማ ክልል የጋራምባ ተራራ ማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ ማቋቋም መቻሉ፣
- ከሀገር ወጥተው የነበሩ የማንነታችን መገለጫ የሆኑትን ታሪካዊ ቅርሶቻችንን ወደ ሀገራችን ለማስመለስ 1 ቅርስ ታቅዶ 17 ቅርሶችን ማስመለስ መቻሉ፣
- የዱር እንስሳትና መኖሪያ አካባቢያቸውን ደህንነት የመጠበቅና የመንከባከብ ሥራን በቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ለማድረግ በተፈጠረው ሀገራዊ ግጭት ምክንያት ሙሉ በሙሉ ስራው ያልተጠናቀቀ መሆኑ ቢገለፅም ከሀገሪቱ ሁኔታ አኳያ በችግር ውስጥ ሆኖ የተሰራው ስራ በበጎ ገፅታው የሚታይ ሆኖ የስራው አፈፃፀምም ከእቅዱ አንጻር ሲመዘን የእቅድ 95 በመቶ መከናወኑ፣
- የተጀመረው አንድ ሀገር አቀፍ የቱሪዝም መዳረሻ አስተዳደር ስርዓት (DMIS) ተጠናቆ ስራ ላይ ለመዋል መቻሉ፣
- በነባር የቱሪስት መዳረሻዎችን ሳቢና ተወዳዳሪነትን የመጨመር ተግባራት በእቅድ የታያዙ ሲሆን በስድስት ወራት ውስጥ በአራት ነባር መዳረሻዎች ላይ የተሰራ ሲሆን ይህም ስራው በ6 ወራት ውስጥ ከግማሽ በላይ መሰራቱ አበረታች መሆኑ፣

- አንድ የቱሪዝም ጋይድ ቡክ ማዘጋጀት ታቅዶ የተለዩ የኢንቨስትመንት አማራጮችን፣ የኢንቨስትመንት ቦታዎችና የተለያዩ መረጃዎችን ለኢንቨስተሩ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ዳታዎችን የያዘ የኢንቨስትመንት ፕሮፋይል አሳትሞ ወደ ስራ ማስገባት መቻሉ፣
- ያልተረጋጋ ፖለቲካ ቢኖርም የሀገርን ገፅታን ገንብቶ ኢንቨስትመንትን ከመሳብ አኳያ በባለኮከብ ሆቴል፣ ሬስቶራንትና ሎጅ ዘርፎች በተለያዩ የአገራችን ከተሞችና የቱሪስት መዳረሻዎች ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ 5 አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን ወደ ዘርፉ ለማስገባት ታቅዶ ወደ 15 በማሳደግ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች ዘርፉን እንዲቀላቀሉ ማድረግ መቻሉ፣
- ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ የቱሪዝም ገበያ ተወዳዳሪ መሆን ካለባት የተለያዩ ገበያ ፍላጎት (market segments) መሰረት ያደረጉ እና የኢትዮጵያ ብዙሃ የቱሪዝም ሀብትና የተለያዩ ጉብኝት መስመሮች ታሳቢ የሚያደርጉ ለአገር ውስጥና ለውጪ ጎብኚዎች ተደራሽ የሚደረጉ 5 ልዩ ልዩ የፕሮሞሽንና ግብይት ፓኬጆች ለመቅረፅ ታቅዶ በአምስት የጉብኝት መስመሮች የተከፈሉ 13 ፓኬጆችን መቅረፅ በመቻሉ ከታቀደው በላይ መከናወኑ፣
- የብራንድ ካምፔን ለማስተዋወቅ እንዲያስችል ከቦሌ ኤርፖርትና አዲስ አበባ መስተዳድር ጋር የተሰራው ቅንጅታዊ አሰራር አበረታች መሆኑ፣
- የጠቅላይ ሚኒስትራችን ወደ ሀገር ቤት እንዲገቡ የተደረገውን ጥሪ ተከትሎ በውጭ የሚኖሩ ኢትየጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ወደ አገራቸዉ ሲገቡ በልዩ ሁኔታ ተቀብሎ ለማስተናገድ እና የተለያዩ የቱሪስት መስህቦችና መዳረሻዎችን በመጎብኘት የተሳካ የቆይታ ጊዜ እንዲኖራቸው ለማስቻል ዲያስፖራ ማህበረሰቡን የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እንዲያነቃቁ የተሰራው ስራ በእቅድ ውስጥ ባይካተትም ስራው አበረታች መሆኑ፣
- በአገር ውስጥ የጉብኝት ባህል እንዲዳብርና ቱሪስቶች አገራቸውን እንዲያውቁ ከማድረግ አንፃር የአገር ውስጥ ቱሪስቶችን ፍሰት 8.22 ሚሊዮን ለማድረስ ታቅዶ የተገኘው ውጤት 10,386,284 መሆኑ በጥንካሬ የተገመገመ ነው፡፡

## <u>በዕጥረት የታዩ ጉዳዮች</u>

- በአጠቃላይ ሪፖርቱ የሪፖርት ማጠቃለያ የሌለውና የሪፖርት ቅደም ተከተልን ያልጠበቀ የጥራት ችግር ያለበት ከመሆኑም በላይ አንዳንድ ተአማኒነት የጐደላቸው ጉዳዮችም ቀርበዋል፡፡ በተጨማሪ እቅዱ ፖቴንሻልን መሠረት አድርጐ የታቀደ አለመሆኑ እና የተጋነኑ አፈጻጸሞችን ያቀረበ መሆኑ

**ለምሳሌ፡-** ታሪካዊ ቅርሶችን ወደ ሀገራችን ለመመለስ 1 ታቅዶ 17 መፈጸም

- የቱሪዝም ተቋም እንደሀገር የሥራ እድል ፈጠራ ላይ ትልቅ ተጽእኖ ይፈጥራል ተብሎ የታሰበ ቢሆንም ፈጽመናል ብለው ካቀረቡት አፈጻጸሞች አንጻር ለሩብ ዓመቱ 100,000 የሥራ እድል እንፈጥራለን ተብሎ የታየዘ ቢሆን የተፈጸመው ግን 23,540 ብቻ በመፈጸም በፐርሰንት 11.77 በመሆኑ ዝቅተኛ አፈጻጸምን ያሳያል፡፡
- የካፒታል በጀት አመዳደብ ያላገናዘበ መሆኑ እና ከግምት ያልዘለለ እና በ6 ወሩ ምንም አፈጻጸም የሌለው መሆኑ፡
- የተቋሙ መደበኛ በጀት አጠቃቀም ከተቋሙ ዋና ዋና ግቦች አፈጻጸም ጋር ያልተጣጣመ መሆኑ፣
- በአገራችን የሚገኙ የማይዳሰሱ ቅርሶችን በአግባቡ ማጥናት፣ መመዝገብና በሰነድ መያዝ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲታወቁና እንዲለሙ ከማድረግ አንፃር በ ግማሽ አመቱ የአሸንዳ፣ አሸንድዬ፣ አይነዋሪ፣ ማርያ፣ ሻደይ፣ ሶለል የኢትዮጵያ ልጃገረዶች ክብረ በዓልን በዩኒስኮ ለማስመዝገብ ተቅዶ በተጠናቀረው መረጃ ላይ ዩኔስኮ የሰጠው ግብረ መልስ ተጨማሪ መረጃ የማሟላት ስራዎች የተፈለገ በመሆኑ **90%** የተጠናቀቀ ስራ ተደርጎ ሪፖርት መደረጉ በተጨማሪ የተገመገመው ውጤት ሳይሆን ሂደት መሆኑ፣
- ቅርስን ጠብቆና ተንከባክቦ ለትውልድ ከማስተላለፍ አኳያ አራት (4) የጥበቃና የእንክብካቤ ተግባራት ለማከናወን ታቅዶ ሶስቱን ቅርሶች ላይ የጥበቃና እንክብካቤ ስራዎች መከናወናቸው በሪፖርቱ የተገለፀ ቢሆንም
    1. በኢሉባቦር ጎሬ ከተማ የሚገኘው ጥንታዊ የእንግሊዝ ቆንስላ ፅ/ቤት ጥገና ስራ በ2014 በጀት አመት ያልተሰራ እና የቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ስራውን ከእቅድ ጋር በማነፃፀር ባልተሰራ ስራ ላይ አፈጻጸሙ 100% ተደርጎ መያዙ፣
    2. የጅማ አባጅፋር የቤተ-መንግስት ጥበቃና እንክብካቤ ስራ ማስጀመር በእቅድ መያዙ የሚታወቅ ሲሆን የጥገና ስራው ቢጀመርም ያልተጠናቀቀና አፈጻጸሙም 100 ፐርሰንት ተደርጎ መያዙ፣
- በቅርስ ጥበቃ ባላስልጣን መስሪያ ቤት የተገኙ የኦዲትና የመንግስት ንብረት አያያዝ ላይ በዋና ኦዲተር እና በመንግስት ወጪ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በተሰጡ የኦዲት ማስተካከያ እርምቶችን በወቅቱ አለማስተካከሉና አግባብነት የሌላቸው አሰራሮች ጎልተው መታየታቸው፣

- ሀገራዊ ቅርሶቻችንን በዩኔስኮ በአለም ቅርስነት ለማስመዝገብ እንዲያስችል ዲስክሪፕሽን የተዘጋጀለት የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል በጌዴኦ ዞን የሚገኘው የጌዲኦ ባህላዊ መልክዓ ምድር ሲሆን አፈፃፀሙ በሪፖርቱ እንደተጠናቀቀ መቅረቡ፣
- የብሔራዊ ፓርኮች ተደራሽነት ከማሳደግና ተወዳዳሪነታቸውን ከማጎልበት አንፃር የመሰረተ ልማት አውታሮች ግንባታ ሥራ ላይ 12 ኪ.ሜ የውስጥ ለውስጥ አዲስ የበጋና ክረምት መንገድ የተሰራ ቢሆንም የመሰረተ-ልማት ሽፋን ከሚያጠቃልላቸው እንደ ዘመናዊ የመጓጓዣ አገልግሎቶች ልማት፣ የቴሌኮሙኒኬሽንና ተያያዥ አገልግሎቶች ልማት፣ የጤናና መሰል የቱሪስቱን ምቾትና ደህንነት የሚጠብቁ አገልግሎቶች ያላካተተ እና ነጠላ ድርጊት ሁሉን ያቀፈ አፈፃፀም ተደርጎ መገለፁ፣
- ህገ ወጥ የዱር እንስሳትና ውጤቶች ዝውውር ለመቆጣጠር የተዘረጋ የአነፍናፊ ውሻ ቁጥጥር ስርዓትን በተመለከተ የውሾች ማቆያ ቤት ግንባታ ዲዛይን ተግባራት የተጠናቀቁ ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት ቀደም ሲል በተፈፀመው ስምምነት መሰረት የግንባታ ቦታ በወቅቱ መቅረብ እንዲችል የተደረገው ክትትልና ቅንጅታዊ ስራ ውስንነት መኖሩ፣
- ፓርኮችና ጥብቅ ቦታዎች ከሕገ-ወጥ ሰፋሪዎች ከመከላከል አኳያ የተሰሩ ሥራዎች በሪፖርት አለመካተታቸው፣
- በዓለም አቀፍ ገበያ ያለንን ተወዳዳሪነት በማሳደግ አዳዲስ መዳረሻዎችን ለማልማት በ6 ወሩ ውስጥ አራት (4) አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችን ለማልማት የታቀደ ቢሆንም የሁለት መዳረሻዎችን ብቻ ማልማት መቻሉ፣
- የኹነት አዘጋጆች እና የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ አማካሪ ድርጅቶች በአጠቃላይ ለ43 የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት የድጋፍ፣ ክትትልና የሱፐርቪዥን ስራዎች ለማከናወንና እውቅና ለመስጠት ታቅዶ በዚህ መቶ ቀን 47 ተቋማት እውቅና እንዲያገኙ ቢደረግም የተቀመጠው የእቅድ ሪፖርት አፈጻጸም ከ100% በላይ መሆኑ ቢገለፅም 93,858 ብር ገቢ መገኘቱ ከእቅዱ አንጻር ሲለካ የተቀመጠው ውጤት 48.9 በመቶ ሲሆን የሪፖርት አፈፃፀም ውጤቱና ከእቅዱ አንጻር ሲለካ የተቀመጠው ሚዛናዊ አለመሆኑ፣
- በዘርፉ የዲጅታል አሰራሮችን በማስፋፋት የፕሮሞሽን ስራዎችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን በሁለት ክልሎች ብቻ ማለትም የቱሪዝም ቢሮዎችን አማራ እና ሲዳማ ድረ-ገፆች ደረጃቸውን በጠበቀ መልኩ መዘጋጀታቸው የተገለፀ ቢሆንም የስራ አፈፃፀሙ ከእቅዱ አንፃር የተቀመጠው ውጤት 100 ፐርሰንት መባሉ ግነትን የሚያሳይ መሆኑ፣

- የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱ ላይ የተቀመጠው የአፈፃፀም ውጤት የተጋነነ፣ እርስ በርሱ ያልተጣጣመና በበጀት አመቱ ያልተሰሩ ስራዎችን እንደተሰሩ አድርጎ የሚያሳይ መሆኑ፣
- የወደሙና የተዘረፉ ቅርሶችን በማስመለስና መልሶ በመገንባት ዳግም የሀገርን ገፅታ ገንብቶ ዘርፉን ለማሳደግ በበቂ ሁኔታ አለመስራቱ፣
- የውጪ ሀገር ቱሪስት ፍሰት ያለው አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆኑ

## ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

ከላይ በዕጥረት የተገመገሙ ተግባራትን ትኩረት በመስጠት በሶስተኛው ሩብ ዓመት ዕቅድ ሪፖርት አፈፃፀም ተካቶ መፈጸም ያለበት፤

- በዓመታዊ እቅድ የታቀዱትን ስራዎች ሳያንጠባጥቡ ትኩረት ሰጥቶ በዕቅድ መሰረት ለመፈፀም መትጋትና ፈፃሚንም ማትጋት ያስፈልጋል፣
- ዘርፉ በአዲስ መልክ እየተደራጀ ከመሆኑ አንጻር በተለይ የሀገር ገጽታ ግንባታንና የብልጽግና ጉዞ ራዕይን ባገናዘበ መልኩ የቱሪዝምና ደጋፊ ተቋማትን የማዘመን፣ ተወዳዳሪ ቱሪዝምን በመፍጠር የመረጃ ሥርዓትን ማላቅ፣ ተቋማዊ የአቅም ግንባታን በማጠናከር የማህበረሰብ ትስስር ተጠቃሚነትን ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በማዋሀድ ከግብ ለማድረስ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት አለበት፣
- ቱሪዝም በኮቪድ 19 ምክንያት በዓለምም ይሁን በሀገራችን ከፉኛ የተመታ በመሆኑ በሀገራችን የፖለቲካ አለመረጋጋት መፈጠሩ ወደፊት የዓለም ሀገራት በራቸውን መክፈት እንዲችሉ ከፍተኛ ክትትል በማድረግ ለሀገራችን የተነደፈውን ማገገሚያ ስትራቴጂ በቅርበት ድጋፍ በማድረግ መሰራት አለበት፣
- የወደሙ እና የተዘረፉ ቅርሶችን መልሶ በመገንባት እና በማስመለስ ዳግም የሀገርን ገፅታ ገንብቶ ዘርፉን ለማሳደግ በትኩረት መሠራት አለበት፣
- ሀገራችን ያላትን የቱሪስት መዳረሻዎችን ለይቶ የማወቅ እና ዶክመንት የማድረግ ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት መሠራት አለበት፣
- ገበታ ለሀገር ፕሮጀክት ላይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ያለው ክትትልና ድጋፍ በትኩረት መሠራት አለበት፣
- ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የክልሎችን አፈጻጸም በመከተታተል እና በመደገፍ ያለውን ሀላፊነት በአግባቡ መወጣት አለበት፣
- የሚሰበሰበው ገቢ ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ተመጣጣኝ የሆነና የፋይናንስ ሥራዓቱን በጠበቀ መልኩ የሚተዳደር መሆን አለበት፣

- ቱሪዝምን ሀገሪቱ ከሰጠችው ትኩረት አንጻር የቱሪዝምን ግብይት በማዘመንና በማቀላጠፍ ተገቢውን የኢኮኖሚ ድርሻ እንዲወጣ መሠራት አለበት፣
- ሪፖርቱ ጥራቱን የጠበቀ እና ትክክለኛ የሪፖርትን ፎርማት የተከተለ ታአማኒነት ያለው ሪፖርት መላክ አለበት፣
- እንክብካቤ ያላገኙ ነባር ቅርሶችን ከመጠገን አኳያ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት ትልቅ ትኩረት መሠጠት አለበት፣ **ለአብነት አልፋ ቪላ**
- የሀገሪቱ ትልቅ ነቀርሳ የሆነውን ሙስናን ብልሹ አሠራሮችን ከመቅረፍ አኳያ አስፈፃሚ መ/ቤቱ በስሩ ባሉት ተቋማትና ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት አለበት፣
- በቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን መስሪያ ቤት ላይ በተገኘው የኦዲት ሪፖርት ግኝት ለቀጣይ እርምት ተገቢውን ማስተካከያ በማድረግ የመንግስት ንብረቶችን ባግባቡ መዝግቦ በመያዝና ገቢንና ወጪን ባለው መመሪያ መሰረት ማስተዳደር ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፣ በተጨማሪም ተጠያቂነት የሚሰፍንበት አሰራር መቀመጥ አለበት፡፡
- የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱ ላይ የተቀመጠው የአፈፃፀም ውጤት የተጋነነ መሆኑ፣ በበጀት አመቱ ያልተሰሩ ስራዎችን እንደተሰሩ አድርጎ የሚያሳይ በመሆኑ በሪፖርት አሰራሩ ላይና በመረጃ አጠነቃቀሩ ላይ እርምት መወሰድ አለበት፣

## ማጠቃለያ

ቱሪዝም ሚኒስቴር አሁን ላይ ችግሮችን በመለየት በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት እየተሰራ ያለው ተግባር ተስፋ ሰጭ ቢሆንም በሀገራችን የቱሪዝም ኢንዱስትሪው በኮቪድ 19 በሽታና በፖለቲካ አለመረጋጋቱ ክፉኛ የተመታ በመሆኑ ሀገራችን ከዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆንና የሚገጥመንን ችግር ቀድሞ በመገንዘብ የመፍትሄ አቅጣጫ እያስቀመጡ በመሄድ የወቅቱ ዋነኛ ትኩረት መሆን ይኖርበታል።

በሌላ በኩል በእቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱ ላይ በጥንካሬ የተጠቀሱትን የበለጠ በማዳበር በዕጥረት የተገመገሙት ላይ ትኩረት ሰጥቶ ለመፈፀም በመትጋትና ሊፈጸሙ የሚችሉበትን መንገድ በማመቻቸት ሊሰራባቸው ይገባል፡፡ የተጠቀሱትን ነጥቦችና ሌሎች እቅዶችንም ፈጥነው ወደ ተግባራዊ አፈጻጸም በመግባት የተፈጠሩ ችግሮች እንዲስተካከሉ ቋሚ ኮሚቴው ይህንን ግብረ መልስ ሰጥቷል።